# አዳራሽ አጋቾች ይታወቃሉ !!!

መጪው ዕሁድ የካቲት አንድ ባልደራስ ለእዉነተኛ ዲሞክራሲ መስራች ጉባኤውን ያደርጋል።

ምርጫ ቦርድ ለጉባዔው ተወካዩን እንዲልክ ለማድረግ የስብሰባ አዳራሽ የሚያከራዩ ሆቴል የከተማው አስተዳደር ድጋፍ ደብዳቤ መፃፍ አለበት የሚል አሰራር መኖሩ የሚገርምም የሚያሳፍርም ነው።

በመሆኑም የምርጫ ቦርድ ሁኔታውን በቢሮው በመሄድ ማሳወቁ የተገባ ነበር። ምርጫ ቦርድም የከተማው አስተዳደር የመሰብሰብን መብት ለማገት የሚያደርገውን አሰራር መቃወም ይኖርበታል።

ብርቱካን ሜዴቅሳ የጃዋር መሀመድ ዜግነት ጉዳይን አስመልክታ ምርጫ ቦርድ የፃፈውን ደብዳቤ አስመልክታ በብዙሀን መገናኛ እንደተናገረችው ለታከለ ኡማ በይፋ መልዕክት ሊደርሰው ይገባል።

በአዲስ አበባ ለጉባኤ ምስረታ አዳራሽ የሚከለክለው የታከለ ኡማ አስተዳደር በአስቸኳይ ከዚህ ድርጊቱ ቢቆጠብ ከሚመጣው ቀዉስ ተጠያቂነት ይድናል።

ታከለ ኡማ አሻፈረኝ ካለ  ኢትዮጵያ ዉስጥ ምርጫ ለማድረግ አለመቻሉን አዲስ አበባ በምስክርነት ተቀምጦ ሀገር ዐቀፍና ዐለም ዐቀፍ ተቃዉሞ ይቀጥላል።

ምርጫ ቦርድ ይህን ለማስፈፀም የማይችልበትን ምክንያት አስረድቶ የድርጅቱ አመራሮች ስልጣናቸውን በመልቀቅ እራሳቸዉን ከ አጋቾች ወገን አለመሆናቸዉን ሊያስመስክሩ ይገባል።

**Tedla Asfaw**